# የለውጡ ጎዳና

በኢትዮጵያ የተከሰተው የለውጥ ሂደት ባልተጠበቀ መንገድ ተጀምሮ በፈጣን ግስጋሴ እየተጓዘ ይገኛል። የለውጡ ሃዋርያ ወጣቱ ትውልድ ነው። ወጣቱ በህይዎቱና በደሙ የከፈለው መስዋዕትነት የምናየውን ለውጥ ወልዷል። ፈጣሪ መረዋ ጩኸቱን ሰምቶ የደም ዋጋውን በዶ/ር አቢይ ከፍሎታል። ዶ/ር አቢይ ወደ ስልጣን በመጡ መቶ ቀናት ውስጥ ዕውን ይሆናሉ ተብለው የማይታሰቡ ክንውኖች ተከናውነዋል።

በህዝቡ መሃል አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል። በዘውጌዎች መሃል የነበረው ጥላቻ እረግቧል። በሃይማኖቶች መሃል የነበረው ክፍፍል ወደ አንድ እየመጣ ነው። ዕስር ቤቶች አምቀዋቸው የነበሩትን እስረኞች ነጻ እንዲወጡ የበሮቻቸውን ቁልፍ ፈትተዋል። አፋኝ ህግጋት ተሽረዋል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተነስቷል። ዘረኝነት ሀዘን ለሀዘን ተቀምጧል። የዜጎች ሰብአዊ መብቶች መከበር ጀምረዋል። ይቅርታና መደመር የገሪቱ የፖለቲካ አግማስ ሆነዋል። ፍቅርና ሰላም በተስፋይቱ መሬት ችግሮቻቸውን ተክለዋል። እናት ኢትዮጵያ ዳግም ብሥራት አግኝታ ከሁለት የተከፈሉት ልጆቿ ወደ አንድነት በሚወስደው ጎዳና ላይ ሲተሙ ተስተውሏል። መረብ በላይንና መረብ በታችን አጥሮ የነበረው ግንብ ፈርሷል። የህዝቡ የማንነት መታወቂያ ሰንደቅም በመላው ግዛቷ ከፍ ብሎ መውለብለብ ጀምሯል። የቀረው ጥቂት ነው።

**ሀ. በመንግሥት በኩል** ባለፉት አርባ ዓመታት በምድረ ጦቢያ ያልተፈፀመ ግፍ አልነበረም። ቀይ ሽብር፣ ነጻ እርምጃ፣ አፈና ዕመቃ፣ ስየል፣ አፍኖ መዳራሻን ማጥፋት . . . በንጹህ ዜጎች ላይ ተፈጽሟል። ድርጅት ከድርጅት ጋር፣ ኃይማኖት ከኃይማኖት ጋር፣ ክልል ከክልል ጋር ተቃቅሯል።ደም የፈሰሰባቸውና የሰው ህይዎት የጠፋባቸው ግጭቶችም ብዙ ናቸው። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንድን ዘር በሌላ ዘር በማስነሳት የዘር ማጥፋት ወንጀል በስፋት ተካሂዷል። ዜጎች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። ያፈሩት ሀብትና ንብረት ተዘርፎ ወደ ድህነት ዓለም ገብተዋል። ስደት የህዝቡ የቀን ተቀን ተግባር ሆኖ ለዓመታት ዘልቋል። የሰው ልጅ እንደ ባሪያ በህግ ስም ተፈንግሏል። ዜጎችን በመሸጥ ራሳቸውን ያበለፀጉ ሰዎች ብዙ ናቸው። እነዚህንና መሰል ወንጀሎችን የፈጸሙ ሰዎች በህይዎት አሉ።

በደሉ ህይዎት ከነፈጋቸው በመለስ በመሞትና በመኖር መሃል የምትናውዝ ህይዎት የሚኖሩትን እናቶች ብዙ ጎድቷል። እናም መንግሥት የጀመረውን የይቅርታ አድማስ አስፍቶ አንድ የዕርቅና የይቅርታ ጉባኤ በማዘጋጀት የተበዳዮቹን ዕምባ ሊያብስ የሚችል ፍትህ ማስፈን ይጠበቅበታል። እንደ ስምምነቱ ውጤትም ፍትሁ በሚደነግገው ውሳኔ የተበደሉ ዜጎች ተክሰው የበደሉ በዳዮችም ለፍርድ ቀርበው አለያም በይቅርታ ያለፈው ቁስል መጠገግ ይኖርበታል። ዘላቂ ሰላም የሚመጣውም ፍትህ በተግባር ሲተገበር ብቻ ስለሆነ መንግሥት ገለልተኛ የፍርድ ተቋም መሥርቶ ፍትህን በአገሪቱ ማስፈን ይጠበቅበታል።

**ለ. ክልልን በሚመለከት** ክልል ሌላው የዘር መጥፋፋት መደላድል ሆኖ ብዙ ጉዳት አድርሷል። የወደፊቱን መንግሥት ለመመስረት ተፎካካሪ ድርጅቶች በሰላማዊ ትግል ራሳቸውን አደራጅተው ለምርጫ ውድድር ይቀርቡ ዘንድ የተዘረጋው የፖለቲካ ማዕድ የክልልን ጉዳይ አጽንኦት ሰጥቶ ሊወያይበት ይገባል። ተፎካካሪ ድርጅቶችና መንግሥት የፓርቲዎችን የአደረጃጀት መልክና ቅርጽ እስካሁን በነበረው የክልል/የዘር አደረጃጀትና የበህብረ-ብሔር አደራጃጀት ጉዳትና ጥቅም በሰከነ ውይይት ዕልባት ሊያበጁለት የግድ ነው። ይህ እሳቤ ከወዲሁ መስመር ካልያዘ ወደፊት ሊደረግ የታሰበው ምርጫ ፋይዳ

አይኖረውም። ስለሆነም የውይይቱን መድረክ አመቻችቶ ችግሩን መልክ ማስያዝ ለነገ የማይሉት የተፎካካሪ ኃይሎችና የመንግሥት የቤት ሥራ ነው።

**ሐ. በተፎካካሪዎች በኩል** ተፎካካሪ ድርጅቶችም ከፍ ብለው የጠቀሱትን ነጥቦች ታሳቢ ያደረገ አስተዋጽኦ ለማበርከት ቅንነት የተሞላበት ኃላፊነት ሊኖራቸው ይገባል። ስለሆነም ቂምና ቁርሾን በይቅርታ አስወግደው ሁሉም ለአገር ግንባታ ድርሻ ድርሻውን ለማበርከት የለውጡ አካል እንዲሆን ይጠበቅበታል። ዛሬ በዘውጌም ይሁን በአገር አቀፍ መልክ የተደራጀው የስብስብ ብዛት ቁጥሩ ቀላል አይደለም። በዚህ ቁጥርም ተፎካካሪ ሆኖ ለምርጫ መቅረብ ከተጀመረው ለውጥ ጋር ተጣጥሞ የሚጓዝ አይሆንም። ስለሆነም ኢህአዴግ ተዋህዶ አንድ ፓርቲ ቢሆንና፣ ሌሎቹም ቡድኖች የሚመስሏቸውን እየፈለጉ ቢዋሃዱና በአገሪቱ የሚኖሩት ተፎካካሪ ፓርቲዎች ቁጥራቸው ከአራት ባይበልጥ ይመረጣል። ከሶስት በታች ግን መውረድ የለበትም።

**መ. የቀጣዩን መንግሥት አውቃቀር በተመለከተ** በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት አማራጮች ሊቀርቡ ይችላሉ።

1. ኢህአዴግ በስልጣን ላይ እንዳለ የምርጫ ህጉንና ምርጫ ቦርዱን አሻሽሎ በቅርቡ ምርጫ ማካሄድ

2. ኢህአዲግ ከስልጣኑ ወርዶ የምርጫ ህጉንና የምርጫ ቦርዱን አሻሽሎ ከሁሉም ወገን የተውጣጣ የሽግግር መንግሥት ማቋቋምና ህገ መንግሥቱን አሻሽሎ በምርጫ ቋሚ መንግሥት መመስረት ነው። የመጀመሪያው ምርጫ ሁሉንም የሚያስማማ አይሆንም። ሁሉንም በስምምነት ሊያራምድ የሚችለው ሁለተኛው ምርጫ ስለሆነ መንግሥትና ተፎካካሪ ኃሎች በዚህ ጉዳይ ላይ ከወዲሁ ሊያስቡበት ይገባል።

**ሠ. የፌደራል አወቃቀርን በተመለከተ** አሁን ያለው የፌደራል ሥርዓት በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም ነው። ይህ አወቃቀር ያስከተለውን ችግር ታሳቢ በማድረግ የፌደራል ቅርጹ ለአስተዳደር ቀና በሆነ መልኩ የመልክዓ ምድርንና የኢኮኖሚ ትሥሥርን መሠረት ያደረገ በክፍለ ሀገር ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም ማቋቋም ፍትሃዊና ቀጥተኛ መስተዳድር ሊሆን ይችላል። አፋርን፣ ጋምቤላንና ኦጋዴንን ግን ራስ ገዝ ማድረግ ተገቢ ይመስለኛል።

እነዚህንና ሌሎችንም ነጥቦች ያካተተ ውይይት በመንግሥትና በተፎካካሪ ሃይሎች መሃል ከወዲሁ እንዲጀመር ተፎካካሪዎቹ ግፊት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በውይይቱ የዳበሩትን የጋራ አመለካከቶች መሰረት አድርጎ ፖሊሲዎችንም መቅረጽ ስለሚቻል ለጉዳዩ ትኩረት መስጠቱ አይከፋም። ህገ መንግሥቱንም በዚሁ በዳበረው የጋራ ግንዛቤ ላይ አስመርኩዞ ማሻሻል የሚቀል መሰለኝ። ለማንኛውም ውይይቱ ይጀመር።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ከጠላቶቿ ይጠብቃት።

ሃምሌ 2010

አብርሃም በየነ

Aderaj3106@gmail.com